# የህሊና እስረኛዋ ብርቱካን ሚደቅሣ በህይወት የመኖር መብት ይከበር!

### ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

### የተሠጠ መግለጫ

የፓርቲያችን የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ሊቀመንበር የሆኑት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ ከህግ አግባብ ውጭ ወደ ወህኒ በማን አለብኝነት ከተወረወሩ ከአንድ ዓመት በላይ ሆኗቸዋል፡፡

ይህንን ኢ-ሠብአዊና ህገወጥ እስር እና አያያዝ የሚመሩት ፓርቲያቸው፣ በሀገር ውስጥና ውጭ የሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎች፣ ሂውማን ራይትስ ዎችና አምንስቲ ኢንተርናሽናል ድርጊቱን ከማውገዛቸውም በላይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ መጠየቃቸው ይታወሳል፡፡ የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብት ጉባዔ የወ/ሪት ብርቱካንን እስር ከሕግ ውጭ በዘፈቀደ እንደተፈፀመ ይፋ ማድረጉ ይታወቃል፡፡ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤትም በቅርቡ ባወጣው የሰብአዊ መብት አያያዝ ሪፖርት ወ/ት ብርቱካን የፖለቲካ እስረኛ መሆናቸውንና የኢትዮጵያ መንግስት እንዲፈታቸው መጠየቁ ይታወሳል፡፡

መንግሥት ይህን ሁሉ የዓለማቀፍ ማህበረሰብ እና የኢትዮጵያውያን ጩኸት ጆሮ ዳባ ልበስ ማለቱ ሳይበቃው የህገ መንግሥቱን አንቀጽ 21 በመጣስ ከዚህ በፊት ባልታዪ ሁኔታ ወ/ት ብርቱካንን ከእናታቸውና ከህፃን ልጃቸው በስተቀር ወዳጅ ዘመድ፣ የሀይማኖት አባት፣ ጠበቃም ሆነ የግል ሀኪም እንዳይጎበኛቸው በመከልከሉ በግፍ ከታሰሩበት ጊዜ ጀምሮ ስለ ጤንነታቸው ሁኔታ መረጃ ለማግኘት ያለንን እድል እጅግ የጠበበ አድርጎታል፡፡

ወ/ት ብርቱካን በይቅርታ ከመፈታታቸው በፊት በእስር በቆዩባቸው 18 ወራትም ሆነ ከተፈቱ በኋላ እንደገና እስከታሠሩበት ጊዜ ድረስ የነበራቸው የጤንነት ደረጃ የተሟላና አስተማማኝ እንደነበር ይታወቃል፡፡ በድጋሚ ከታሰሩ በኋላ ግን በተለይም በቅርቡ ጤነታቸው መታወኩን ከወላጅ እናታቸው በመስማታችን እጅግ አሳስቦናል፤ አስደንግጦናል፡፡

የወ/ት ብርቱካን ህይወትም ሆነ እጅግ አሳሳቢው የጤንነታቸው ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት እጅ እንደመገኘቱ ኃላፊነቱም በግፍና በማን አለብኝነት አስሯቸው የሚገኘው

መንግሥት መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሁም የዓለማቀፉ ማህበረሰብ ሁሉ ልብ ሊሉት ይገባል፡፡

የወ/ት ብርቱካን እስር ህገወጥነትና ከዚያም በላይ የጤንታቸው መታወክ ሊያስከትል የሚችለውን ፖለቲካዊ መዘዝ በማጤን መንግሥት የሊቀመንበራችንን መፈታት ጉዳይ በቅን ልቦና ተመልክቶ በጎ ውሳኔ እንዲያሳልፍ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

ይህ ጉዳይ ከቁጥጥር ውጭ ወጥቶ የወ/ት ብርቱካን አሳሳቢው የጤንነታቸው ሁኔታ ህይወታቸው ላይ አደጋ ከማድረሱ በፊት መንግሥት የኢትዮጵያና የዓለም ቀይ መስቀል ማህበራት በታዛቢነት በተገኙበት በገለልተኛና ብቃት ባላቸው የሀኪሞች ቡድን ተገቢውን ምርመራና ህክምና እንዲያገኙ እንዲያደርግና ውጤቱንም ለኢትዮጵያ ለህዝብ ይፋ እንዲያደርግ አበክረን እናሳስባለን፡፡

በፓርቲያችን፣ በኢትዮጵያ ሕዝብና በማንኛውም ሠላም ወዳድ ማህበረሰብ ዕምነት መሠረት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ በፖለቲካ ውሳኔ እንደታሠሩ እሙን ነው፡፡ እንዲሁም በፖለቲካ ውሣኔ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሊፈቱ ይገባል፡፡ መንግሥታትና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች የወ/ት ብርቱካንን ጤንነት መታወክ በሕይወታቸው ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር በመገንዘብ ከዚህ በፊት እንዳያረጉት ሁሉ ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ ከእስር እንዲለቀቁና በገለልተኛና ብቃት ባላቸው ሀኪሞች የህክምና እርዳታ እንዲደረግላቸው አሁንም ያለማሰለስ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ጫና እንዲያሳድሩ እንጠይቃለን፡፡

የተባበሩት መንግስታት ዋና ጽኃፊ ሚስተር ባንኪሙን ጽ/ቤት የወ/ሪት ብርቱካንን ሕገ ወጥ እሥራት ተከትሎ በጤንነታቸው ላይ እየደረሰ ያለውን መታወክ በማጤን እስሩ እልባት ያገኝ ዘንድ ጽ/ቤታቸው ተገቢ ሚና እንዲጫወት አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ህዝብ በወ/ት ብርቱካን ላይ እየደረሰ ያለውን እስርና እንግልት የራሱ የጭቆናና የእስር ተምሳሌት አድርጎ በመውሰድ ለፖለቲካ መሪውና ለህሊና እስረኛዋ ከእስር ነፃ መውጣት፣ጤንነት መጠበቅና ብሎም በህይወት መኖር ይህ ቀረሽ የማይባል ትግል እንዲያደርግ አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

መጋቢት 17 ቀን 2002 ዓም

<u>አዲስ አበባ</u>